የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.32
ADDIS ABABA, 19st April , 2017

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ለማደስ የወጣ አዋጅ……ገፅ ፱ሺ፮፻፮

**<u>CONTENT</u>**

Proclamation No.1004/2017

State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security Renewal Proclamation....page 9606

## አዋጅ ቁ□ር ፩ሺ፬/፪ሺ፱

## <u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ለማደስ የወጣ አዋጅ</u>

የህዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ መስከረም ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ታውጆ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር ፱፻፹፬/፪ሺ፱ ከፀደቀ በኋላ በሕገ መንግስቱና በሕገ መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ የተቃጣውን አደጋ በቁጥጥር ስር ለማዋል ባለፉት ስድስት ወራት በተሰራው ስራ የተገኘውን አንፃራዊ ሰላም እና መረጋጋት ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ ማድረስ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአገራችን አንዳንድ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር እንዲሁም ህብረተሰቡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተፈፃሚነቱ እንዲቀጥል ያለውን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፺፫(፫) እና አንቀፅ ፶፭(፰)

## PROCLAMATION No.1004/ 2017

## <u>THE FEDERAL DEMOCRATAIC REPUBLIC OF ETHIOPIA HOUSE OF PEOPLES' REPRESENTATIVES STATE OF EMEREGENCY PROCLAMTION FOR THE MAINTENACE OF PUBLIC PEACE AND SECURITY RENEWAL PROCALAMTION</u>

**WHERE AS,** the State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security No. 1/2016,issued by the Council of Ministers, on the 8th day of October ,2016 has been approved by the House of the Peoples' Representatives with Proclamation No. 984/2016 ,and it has become necessary to attain irreversible level of the relative peace and security attained as a result of activities performed during the past six months to put under control the danger directed against the constitution and constitutional order;

**WHERE AS,** considering the wish of the people for the continued application of the State of Emergency Proclamation and to control the security problems observed in some parts of our country;

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 93(3) and Article 55(8) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the State of Emergency

መሠረት የህዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለቀጣይ አራት ወራት እንደሚከተለው ታድሷል:-

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ለማደስ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬/፪ሺ፱” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. <u>የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ስለማደስ</u>**

የህዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ እና አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፬/፪ሺ፱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለቀጣይ አራት ወራት ተፈፃሚ ሆኖ እንዲቀጥል በሙሉ ድምፅ ተወስኗል፡፡

**፫.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ለማስፈፀም ወጥተው በስራ ላይ ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

፪/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ እና አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፬/፪ሺ፱ መሰረት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት የተወሰዱ እርምጃዎች፣የተሰጡ ውሳኔዎች፣ በፍትህ አካላት የተወሰኑ ጉዳዮች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ውሳኔዎች በዚህ አዋጅ መሰረት ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

፩/ ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ጀምሮ ለአራት ወራት የፀና ይሆናል፡፡

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ ይህን አዋጅ በመገናኛ ብዙሃን ለህብረተሰቡ ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

Proclamation for the Maintenance of Peace and Security is hereby renewed for the coming four months as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as “State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security Renewal Proclamation No.1004/2017”

**2. <u>Renewal of the state of Emergency Proclamation</u>**

The State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security No.1/2016 is hereby renewed to be applicable for the coming four months with unanimous vote by the House of the Peoples’ Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

**3. <u>Transitory Provisions</u>**

1/ Regulations and directives issued to in force the State of Emergency Proclamation and which are in force shall continue to be applicable.

2/ Measures and decisions taken by the State of Emergency Command Post ,decisions given by judicial bodies and other relevant decisions given in accordance with the State of Emergency Proclamation 1/2016 and Proclamation No.984/2016 shall continue to be applicable.

**4. <u>Effective Date</u>**

1/ This Proclamation shall remain in force for the coming four months from 6th April, 2017.

2/ The State of Emergency Command Post shall declare this Proclamation to the public through the mass media.

**Done at Addis Ababa, this 19th day of April , 2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**